4ኛ ዓመት ቁጥር 15

4[Th] Year No. 15

ሐረር ነሐሴ 24/1991

Harar August 30/1999

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

# ሐረር ነጋሪ ጋዜጣ

# HARAR NEGARI GAZETA

*HARARI PEOPLE NATIONAL REGIONAL STATE*



| የአንዱ ዋጋ ብር 1:00 | በሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ተጠባባቂነት የወጣ | የፖስታ ሣጥን ቁጥር 272 |
|---|---|---|





**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር 20/1991

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሥራ አመራር ኢንስቲትዩት ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ቁጥር 20/1991 ---------------------------------------- ገጽ 176



## አዋጅ ቁጥር 20/1991

## የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሥራ አመራር ኢንስቲትዩት ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

በሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ያለውን የሰው ኃይል እጥረት ደረጃ በደረጃ መቅረፍ ለኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ ዕድገት መቀላጠፍ ያለው አስተዋጾኦ ከፍተኛ ስለሆነ፥

የሰለጠነ የሰው ኃይል ማፍራት የሚቻልበትን መንገድ ለመፍጠር በሥራ ላይ ተሰማርቶ የሚገኘውን የሰው ኃይል የአጭርና የረጅም ጊዜ ስልጠናዎችን በመስጠት የበለጠ አቅም እንዲኖር ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፥

በክልላዊ መንግሥቱ በየደረጃው ተሰማርቶ ለሚገኘው የሰው ኃይል የሚሰጡ ስልጠናዎችን የሚመራ ራሱን የቻለ መንግሥታዊ አካል መመስረት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፥

የሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት በክልሉ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ 2/ሀ/ መሠረት ከዚህ የሚከተለው ታውጇል።

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ

**1. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሥራ አመራር ኢንስቲትዩት ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ቁጥር 20/1991" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**2. ትርጉም**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ ፦

1. "የክልል መንግሥት" ማለት ፦ በሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ ህገ-መንግሥት መሠረት የተመሠረተ የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ነው።
2. "ሥራ አስፈጻሚ" ማለት ፦ በሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ

ሲፈቀድም ተግባራዊነቱን ይከታተላል፣

3. የኢንሲቲትዩቱን የሩብ ዓመት እና ዓመታዊ የሥራ አፈጻጸምና የሂሣብ ሪፖርት ይገመገማል፣

4. ኢንስቲትዩቱን የሚመራ ሥራ አስኪያ መርጦ ለሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በማቅረብ ያሾማል፣

5. የተቋሙ ሂሣብና ንብረት በአግባቡ መያዙን ያረጋግጣል፣

6. ሥራ አስኪያጁ የሚያቀርባቸውን ጉዳዩች መርምሮ ውሣኔ ይሰጣል፣

## 8. ተጠሪነቱ

የቦርዱ ተጠሪነት ለሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ርዕስ መስተዳድር እና ለሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ነው።

## 9.የቦርዱ ስብሰባና አሠራር

1. ቦርዱ በሶስት ወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል። ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በማናቸውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል።

2. የቦርዱ አባላት አብዛኛው ከተገኙ ምልዐተ ጉባኤ ይሆናል፣

3. የቦርዱ ውሣኔዎች በድምጽ ብልጫ ይወሰናሉ ሆኖም ድምጽ እኩል ከተከፈለ ሰብሳቢው ያለበት ወገን ያልፋል፣

4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ቦርዱ የራሱ የስብሰባ ሥነ ሥርዓትና ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

## 10. የሥራ አስኪያጁ ተጠሪነት

የኢንስቲትዩቱ ሥራ አሲኪያጅ ተጠሪነቱ ለቦርዱ ይሆናል።

## 11. የሥራ አስኪያጁ ሥልጣንና ተግባር

የኢንስቲትዩቱ ሥራ አስኪያጅ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 ላይ ኢንስቲትዩቱ የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባራት የሚያከናውን ሲሆን በተጨማሪም የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የኢንስቲትዩቱን ሠራዎች ይመራል ፣ ያስተዳድራል ፣ ይቆጣጠራል ፣

2. በሲቪል ሰርቪስ ደንብና መመሪያ መሠረት የሚያስፈልጉትን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፣

3. የኢንስቲትዩቱን የአጭርና የረጅም ጊዜ ዕቅድ ዓመታዊ የሥራ ፕሮግራምና ባጀት አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል ሲፈቀድለትም ሥራ ላይ ያውላል፣

4. ኢንስቲትዩቱ በተፈቀደለት የሥራ ፕሮግራምና ባጀት መሰረትገንዘብ ወጪ እንዲሆን ያደርጋል፣ በሥራ ላይ መዋሉን ይቆጣጠራል፤

5. ከሦስተኛ ወገን ጋር በሚድረግ ግንኙነት ሁሉ ኢንስቲትዩቱን ይወክላል፣

6. የኢንስቲትዩቱን የሩብ ዓመት ዓመታዊ የሥራ አፈጻጸምና የሒሳብ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፣

7. በቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ሥራዎች ይፈፅማል፡፡

## ክፍል ሦስት

## 12. በጀት

### የኢንስቲትዩቱ በጀት፥

1. በመንግስት የሚመደብና፣

2. በሌሎች ምንጮች በሚገኝ ገንዘብ ይሆናል፡፡

## 13. የሒሳብ መዛግብት አያያዝ

1. የኢንስቲትዩቱ የተሟላና ትክክለኛ የሆነ የሒሳብ መዛግብት ይይዛል፣

2. የኢንስቲትዩቱ የሒሳብ መዛግብትና የገንዘብ ነክ ሠንዶች ለክልሉ ዋና ኦዲተር ወይንም ቦርዱ በሚሰይማቸው የውጭ ኦዲተሮች በየዓመቱ ያስመረምራል፡፡

## 14. ተፈጻሚነት የሌላቸው ህጎች

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም የክልሉ ህግ በዚህ አዋጅ ውስጥ በተመለከቱት ጉዳዩች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም ፡፡

15. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልሉ በሐረሪ ነጋሪ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

ሐረር ጥር 1992 ዓ.ም

ጋዛሊ መሐመድ አዱስ

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ

መንግሥት

ፕሬዝዳንት